ሳምንታዊ ዜና

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ -ጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም.

**በህወሀት ባለስልጣናት መካከል ከፍተኛ ሽኩቻ መኖሩ ተነገረ፤ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ለህወሀት ብቻ የተወሰነ መሆኑ ተጋለጠ፤ ብአዴኖች በበረከትና በአዲሱ አቋም ተበሳጩ በህወሀት አኩረፉ፤ መለስ የሚኒስትሮች ሹም ሽር አደረገ፤ ወያኔ ያስፋፋው ርሀብ እንዳይጋለጥበት ሲል ዜጎችን ከሆስፒታል እውጥቶ በረሀ ላይ አፈሰሳቸው ብርካቶቹ ሞቱ፤ ድርጊቱ የተፈፀመው በመለስ ትዕዛዝ መሆኑ ተጋለጠ፤ የእንግሊዙ ባለስልጣን በተፈጠረው ረሀብ የወያኔን ቡድን ተጠያቂ አደረጉ፤ የተባረሩት የሱማሌ ክልል ባለስልጣናት እና የካቢኔ አባሎችን ለርሀቡ ተጠያቂ ለማድረግ መታቀዱ ተጋለጠ፤ ወደ ሱማሌ ክልል የእርዳታ እህል እንዳይጉዋጉውዝ ወያኔ የከለከለው ለታጣቂ ኃይል ይደርሳል በሚል መሆኑ ታወቀ፤ ሙሉዉን እዚህ ላይ ተጭነዉ ያንብቡ<<<>>>**

የወያኔው ቡድን ቁንጮ ክፍል በሆነው በህወሀት ወስጥ ከፍተኛ ሽኩቻ መኖሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቆሙ::እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ ከህወሀቱ የመቀሌው ጉባኤ ወዲህ እርስ በርስ ንትርክ የጀመሩ ሲሆን፤በተለይም የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን የባሉዋ ዋና አማካሪ በመሆን አብረው ከነበሩት ሰዎች ጋር ሁሉ ቅራኔ ውስጥ እየከተተቸው መሆኑን ገልፀዋል::

በነሐሴ ወር ማብቂያ በመቀሌ ህወሀት ባደረገው ጉባኤ ላይ አርከበ እቁባይና መለስ ዜናዊ ቃላት ሲለዋወጡ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ አሁን ደግሞ ሌሎችም የህወሀት ባለስልጣናት ተጨማምረው ነገሩ ከመብረድ ይልቅ እየተቀጣጠለ እንደሚገኝ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

አቦይ ስብሀት የተባሉት በህወሀት ባለስልጣናት ዘንድ በአባትነት የሚታወቁት እድሜ ጠገብ ሰው በዚሁ በተፈጠረው ውዝግብ ውስጥ ጣልቃ ገብተው አንተም ተው አንተም ተው በማለት ችግሩን ለመፍታትና ብሎም ለመቅረፍ ደፋ ቀና ሲሉ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ምንም ጨዋነት በጎደለው መልክ ሽማግሌውን ያዋረደቻቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ እሳቸውም በንዴት የብልግና ስድብ በመሳደባቸው የተነሳ ነገሩ ከርሮ ለያዥ እና ለገናዥ አስቸግሮ እንደነበረ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

በተለይ የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣን ናቸው በተባሉ ቦሌ አካባቢ መኖሪያ ቤት ካላቸው 3 ግለሰቦች ቤት ውስጥ በተለያዩ ቀናት ጨለማን ተገን በማድረግ እርቅና ሽምግልና ይዘው የነበሩት አቦይ ስብሀት በአዜብ ተሰድበው በደረሰባቸው የሞራል ስብራት ምክንያት ሽምግልናውን ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው የነበረ ቢሆንም ለእሳቸው እንደገና ሽማግሌ ተልኮ ይቅርታ እንዲያደርጉላት ተነግሮዋቸው ሲመለሱ አዜብ ግን የሴትን ልጅ ወግና ባህል ባልጠበቀ ሁኔታ እየተቆናጠረች አሻፈረኝ እንዳለች ምንጮቹ አስረድተዋል::

ከሁለት ወር በፊት በአርከበና በመለስ መካከል የነበረው ውዝግብ ተስፋፍቶ ይዘቱን እየለወጠ መጥቶ መለስን ማን ይተካው? በሚለው ላይ ከሁለት ዓመት በሁዋላ ለሚሆነው ከወዲሁ እርስ በርስ እየተናከሱ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የህወሀት አንደኛው ክፍል አርከበ እቁባይ በአዲስ አበባ ከተማ ሰርቶ ታዋቂነትን አግኝቶዋል:: በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭም የተለያዩ መሪዎች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የነበረ በመሆኑ ለዲፕሎማትነት ስራ ችግር ስለማይገጥመው እሱ ቢሆን ይሻላል ሲሉ ሌላኛው በመለስ የሚመራው ቡድን ደግሞ አርከበ ልምድ ያንሰዋል ስለዚህ ስዩም መስፍን ጥሩ

ነው እሱም ባይሆን ጊዜ ወስደን እንመርጣለን በሚል እርስ በርስ ሽኩቻ ውስጥ እንዳሉም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ገና ከሁለት ዓመት በሁዋላ ለሚደረገው ስልጣን ርክክብ ዛሬ እርስ በርስ እየተባሉ ህዝቡ ግን በየቀዬው የሚቀምሰው አጥቶ እየሞተ ባለበት በዚህ ወሳኝ የህይወት ማዳኛ ወቅት ይህንን ማድረጋቸው የሚያሳዝን ነው ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህር አርከበም መጣ መለስም ወረደ ምንም ትርጉም የለውም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ከመሆን አይዘልም ፡፡ለውጡ ሙሉ ለሙሉ ፓርቲው ስልጣኑን ለቅቆ ለሌላ በሰላማዊ መንገድ ሲያስረክብ ነበር በማለት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

መለስና አርከበ ከበረሀ ጀምሮ ውስጥ ውስጡን ሲባሉ የመጡ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች በተለይ በአንድ ወቅት መለስ ይሰጥ በነበረው ወታደራዊ ትዕዛዝ በተዋጊዎቹ ላይ ከፍተኛ ሽንፈትና ኪሳራ ደርሶባቸው እንደነበርና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሁለቱ የወያኔ ባለስልጣናት መካከል ከፍተኛ ሽኩቻ መኖሩን አጋልጠዋል፡፡

የሁለቱ ባለስልጣናት ሽኩቻ ተስፋፍቶ የሁለቱም ቡድን ደጋፊዎች እየበረከቱ የመጡ ቢሆንም አዜብ መስፍን በተለይ በአርከበ ላይ ባላት ጥላቻ ምክንያት ባሉዋን ሁሉ የማይሆን እርምጃ እንዲወስድበት እየገፋፋችው መሆኑን ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡ የሁለቱንም ወገን እየሸመገሉ ያሉት አቦይ ስብሀት ምንም እንኩዋን በአዜብ መስፍን ስድብ ቢናደዱና አቁዋርጠው ትተውት የነበረ ቢሆንም «መስዋዕት በሆኑ ጉዋዶቻችን» በሚል ተለምነው በድጋሚ ወደ ሽምግልናው የገቡ መሆናቸውንና እሳቸውም ከማሸማገል ይልቅ አቁዋም ወስደው መከራከር መጀመራቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በዚህም ምክንያት መለስ ስልጣኑን ከለቀቀ ቦታውን መያዝ ያለበት ህወሀት መሆንኑን ሁለቱንም ቡድን ያስማማ ሲሆን በሁለቱ ቡድን ግን የቀረበው የግለሰብ ለውጥ ብቻ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የመለስ ቡድን ስዩም መስፍን ይሁን ሲል ሌላኛው የነአቦይ ስብሀት ደግሞ አርከበ እቁባይ በሚለው ብቻ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

እርስ በርስ ውዝግብ ውስጥ የገቡት የወያኔ ባለስልጣናት ቀድሞ በተመደበላቸው ጥበቃዎች ሲጠበቁ የነበረ ቢሆንም ሁሉም አብረዋቸው የነበሩትን ጥበቃዎች አባርረው ሌላ እራሳቸው በመረጡት ወታደሮች እየተጠበቁ እንደሚገኙ ምንጮቹ ጠቁመው ይህ የሚያመላክተው ውስጣቸው የተጀመረው ሽኩቻ እየጋለ መምጣቱን ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡አያይዘውም ምንም ይሁን ምንም ድመት እንደምትደብቀው ሁሉ ህወሀቶችም ልዩነታቸው በይፋ ጎልቶ እንዳይወጣ ብርቱ ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ አንዳችም እንቅስቃሴ እንደሌለ ማስመሰል እንደሚችሉበት ምንጮቹ አስተረድተዋል፡፡

ከጨዋታ ውጭ የሆነው የብአዴን ቡድንም ስልጣን ለኛ ለምን አይገባንም በሚል የሚወተውቱ አፍለኛ ባለስልጣናት ቢኖሩም በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ግን የብአዴን ካድሬና ባለስልጣናትን ቀንድ ቀንዳቸውን እየመቱ አንገታቸውን እንዲደፉና በህወሀት እግር ስር እንዲደፉ እያደረጉዋቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ለ17 ዓመታት የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዴት ሊዘልቅ ይችላል? በማለት አሁንም ጥያቄ እያነሱ ቢሆንም ሰሚ በማጣታቸው ብዙዎቹ የብአዴን ካድሬዎች ማኩረፋቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ከበረሀ ጀምሮ መስዋዕትነት የከፈልነው እኩል ነው እያሉ ብአዴኖች እየወተወቱ ቢሆንም ህወሀቶች ቀድሞም ቢሆን የውሀ ጀሪካን ሲያመላልሱ የቆዩ እንጂ ውጊያ ላይ ተሳትፈው አያውቁም በሚል የሚንቁዋቸው በመሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ከህወሀት እጅ እንደማይወጣ ከወዲሁ ግልፅ እያደረጉት መሆኑ ታውቆዋል።

በተለይ የብአዴን ካድሬዎች የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ በተመለከተ ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዳያነሱ ብሎም ሀሳብ እንዳይኖራቸው ለማድረግ በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ከፍተኛ ስራ ውስጥ ውስጡን እየሰሩ መሆኑን ምንጮቹ ጠቁመዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሐሙስ ሕዳር 20 ቀን 2001 ዓ. ም. በተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የሹም ሽረት ማድረጉን በይፋ ገለፀ።መለስ በዚሁ ባደረገው ሹም ሽረት ብዙ ጊዜ ከስልጣኑ እንደሚነሳ ሲነገርበት የነበረውና በመለስ ጥርስ ተነክሶበታል ተብሎ የሚወራበት ሽፈራው ጃርሶ የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል እንዲሉ ከምክር ቤት የመንግስት ተጠሪነቱ ተነስቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የህዝብ አደረጃጀት የመለስ አማካሪ የነበረው ኃይለማሪያም ደሳለኝ የተተካ ሲሆን ሌሎችም በርካታ ሚኒስትሮች ከቦታቸው እየተነሱ ወደ ሌላ ቦታ እየተቀየሩ መሆኑ ታውቆዋል።

በዚህም መሰረት የማስታወቂያ ሚኒስትር ብርሀን ሀይሉ፣ የፍትህ ሚኒስትር አሰፋ ከሲቶ፣ የትራንፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ጁኔዲ ሳዶ ፣የትምህርት ሚኒስትር ዶ/ር ስንታየሁ አለሙ ፣ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስትር ወ/ሮ ሂሩት ዴሌቦ እና ሌሎችም ከቦታቸው ተነስተው ወደ ሌላ ቦታ የተዛወሩ ሲሆን የጉራጌ ተወላጅ ነው የተባለው ሲራጅ ፈርጌሶ መከላከያ ሚኒስትርነቱን ቦታ እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሎዋል።

በቅርቡ የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት እና ተፈራ ዋልዋን ተክቶ የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር የሆነው ደመቀ መኩሪያ የተባለው አፍለኛ ካድሬ የትምህርት ሚኒስትርነቱን ስልጣን ሲሰጠው አዲስ የተዋቀረው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተብሎ ለሚጠራው ሚኒስትር ጁኔዲ ሳዶ እንዲሆን መመደቡን ለማወቅ ተችሎዋል።

ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ጊዜ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በቅርቡ የባለስልጣናት ሹም ሽረት እንደሚያደርግ አስቀድመን የዘገብን ሲሆን በተባለው መሰረትም በርካታ ሚኒስትሮች ተነስተው በሌላ የተተኩ ቢሆንም በተደገረው ሹም ሽረት አንድም የህወሀት ሚኒስትር ያልተነካ መሆኑ ታውቆዋል።

ለወያኔው መሪ አፋሽ አጎንባሽ ሆነው ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልከዋቸው ወዴት እያሉ ህዝቡን ግራ ሲያጋቡ የነበሩት እነዚሁ ጥቅመኛ የወያኔ ሚኒስትሮች ባላሰቡትና ባልጠበቁት ሁኔታ ገሚሶቹ እንደኩዋስ ጎነው ሲባረሩ ገሚሶቹ እንዳያማህ ጥሬው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ ለይስሙላ ሚኒስትር መስሪያ ቤት እንዲመሩ ተብሎ የመወሰን አቅማቸው ተገድቦ የተመደቡ መሆኑንም ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ገልፀዋል።

በአንድ መምሪያ ውስጥ የደህንነትና የካድሬነት ስራ እንዲሰሩ ሲቪል ሰርቪስ ከሆነው ከወያኔ ተቋዋም የተመረቁ ወያኔዎች በየመስሪያ ቤቱ የተሰገሰጉ ሲሆን ፣ ሚኒስትሮቹን ሳይቀር ከስር ሆነው እንደሚቆጣጠሩና እንደሚከታተሉ ስውር ስልጣን እንደተሰጣቸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

ሰሞኑን የተደረገው ይኸው ሹም ሽር አንድም የህወሀትን ባለስልጣን ያልነካ ሲሆን ኦህዴድ እና በብአዴን በተባለው የወያኔ ተለጣፊ ክፍሎች ላይ ጠንካራ እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ብርሀን ሀይሉ ከማስታወቂያ ሚኒስትርነት ፤ ዶ/ር ስንታየሁ ኃ/ሚካኤል ከትምህርት ሚኒስትርነት ፤ጁኔዲ ሳዶን ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትርነት ፤ሽፈራው ጃርሶን ከምክር ቤት ተጠሪነት አንሳፍፎ ያነሳቸው መሆኑ በወያኔ ውስጥ ከፍተኛ ችግር መኖሩን የሚያሳይ ፍንጭ እንደሆነም ዘገባው አስረድቶዋል።

ሐሙስ እለት በተደረገው በዚሁ ሹም ሽር ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር ተነስቶ የአማራ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ የሆነው አቶ ተፈራ ደርበው የተተካ ሲሆን የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ጁኔዲ ሳዶ የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊው ድሪባ ኩማ የተተካ መሆኑ ታወቆዋል።

የሴቶች ጉዳይ ሚኒስትር ወ/ሮ ሂሩት ዴሌቦ በወያኔ ስራ አስፈፃሚዋ ወ/ሮ መፍሪያት ከሚል የተተካች ሲሆን የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበረው ብርሀን ኃይሉ ከቦታው ተነስቶ የፍትህ ሚኒስትር ሆኖ ተሾሞዋል። የማስታወቂያ ሚኒስትር ከሚኒስትርነት ደረጃ ዝቅ ብሎ በመምሪያ ደረጃ ተዋቅሮ የህወሀቱ ባለስልጣን እንዲመራው እንደተደረገ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

ወጣትና ይሰሩልኛል ብሎ የዛሬ ሁለት ዓመት የሾማቸውን ሚኒስትሮች መለስ ዜናዊ የአይናቸው ቀለም አላማረኝም ብቻ ሳይሆን የህወሀትን የበላይነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ ለመቀጠል ስላቀደና ስለወጠነ አሁን ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን የገለፀው ዘገባው በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወያኔ ውስጥ የተጀመረው ማጉረምረም እየሰፋ በመምጣቱ እረፍት ማግኛ ዘዴ አድርጎ የተጠቀመበት ስልት መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

በነሐሴ ወር ማብቂያ ላይ ህወሀት መቀሌ ፤ብአዴን ባህር ዳር ፤ኦህዴድ አርሲ ፤ደኢህዴን ወላይታ ሶዶ ላይ በተናጠል ባደረጉት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሁሉም ድርጅት ወጣት ካድሬዎች የነሱዋቸው ጥያቄዎች ለመለስ ትልቅ የራስ ምታት ፈጥረውበት እንደነበረ ያስታወሰው ዘገባው በአዋሳው ጠቅላላ ጉባኤ ላይም ቢሆን ተሰብሳቢ ካድሬዎቹ ዘንድ ጥሩ መንፈስ እንደሌላቸው የተረዳው መለስ እንደልብ በሚያሽከረክራቸው አዲሱ ለገሰ እና በረከት ስምኦን ብአዴንን፤ አባዱላ ገመዳና ደግፌ ቡላ ኦህዴድን፤ ኃይለማሪያም ደሳለኝ እና ሽፈራው ሽጉጤ ደኢህዴንን እንልባቸው እንዲወጥሩለት በማድረግ ውስጥ ውስጡን ስራ እሰራ ሲሆን ከዚህ በሁዋላም ብዙ የማባረር ስራዎችን ለመስራት እንዳቀደ ዘገባው አብራርቶዋል።

ወያኔ የተራቡ ወገኖችን እንዳያሳጡኝ በሚል ከቀብረደሀር ሆስፒታል አፍሶ በረሀ ላይ እንደጣላቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ። በቅርቡ የእንግሊዙ ዓለም አቀፍ የልማት ሚኒስትር የሆኑት ዳግላስ አሌክሳንደር በኢትዮጵያ ያለውን የርሀብ ሁኔታ እና እስከ ዛሬ ድረስ የሚሰጡት እርዳታ በአግባቡ ለተረጂው ህዝብ መድረሱን ለማረጋገጥ እና ብሎም ሌላ አዲስ የእርዳታ ስምምነት ለመፈራረም ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ቢሆንም ባዩትና በሰሙት ነገር እጅግ ተበሳጭተው መመለሳቸውን ዘገባው ገልፆዋል።

በአዲስ አበባ ማንንም ባለስጣልን ሳያነጋግሩ ወደ ቀብሪ ደሀር የተጉዋዙት ዳግላስ አሌክሳንደር በሆስፒታሉ በርካታ ረሀብተኛ ወገኖች መኖራቸው አስቀድሞ ተነግሮዋቸው የነበረ ቢሆንም በስፍራው ስደርሱ አንድም ረሀብተኛ ያላገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ እነመለስ ረሀቡን በቁጥጥር ስር ያዋሉት ለማስመሰል አንዲት ህፃን ከነወላጅዋ ከረሀቡ አገግመው በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለማሳየት ተዘጋጅተው የጠበቁዋቸው መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

በስፍራው በተለይ በሱማሌ ክልል ውስጥ በኦጋዴን ፤ ፊርፊር ፤ ቀብሪደሀር እና በሌሎችም አካባቢዎች ለብዙ ዓመታት ያገለገሉ የሲጋሽ ድርጅት ሰራተኞች እንዳሉት ከሆነ ረሀብተኞቹ ሆስፒታል ውስጥ ሲሰቃዩ እንደነበር ለእንግሊዙ ባለስልጣን አሳይተው አጣዳፊ እርዳታ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የሞከሩ ቢሆንም በወያኔው መሪ ትዕዛዝ በቡችላ ካድሬዎቹ ፈጻሚነት በጦር ሔሊኮፕተር ከሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ በማጉዋጉዋዝ ከአካባቢው ራቅ ወዳለ በረሀ የወሰዱዋቸው መሆኑንም ዘገባው ገልፆዋል።

በዚህ ድርጊት የተበሳጩት ዳግላስ ብዙ ቀናት በአካባቢው ተዘዋውረው ለመመልከት አቅደው የነበረ ቢሆንም ባዩት እና በሰሙት ሸፍጥ በመናደድ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የተሰራውን ሸፍጥና ክህደት በግልፅ ከመንገራቸውም በተጨማሪ የእርዳታ ስምምነቱን ከእንግዲህ በአጭር ጊዜ እንደማይፈፅሙ በመግለፃቸው የተደናገጠው መለስ « ድርጊቱን በፈፀሙት ላይ እርምጃ እንወስዳለን» በማለት ቀድሞም ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽ ባላፈርሽ እንዲሉ መጀመሪያ ድርጊቱን እራሱና መሰሎቹ ፈፅመው እንዳልሰሙና እንዳላወቁ ሆነው መቅረባቸውን ዲፕሎማቶቹን ጭምር ያሳዘነና ድካማቸውን ጭምር ከንቱ ያደረገ መሆኑን የዲፕሎማቲክ ምንጮች ሲገልፁ ተደምጠዋል።

በተለይም ረሀብተኛ ወገኖች በየደቂቃውና በየሰከንዱ በያሉበት እንደቅጠል እየረገፉ ባሉበት በዚህ ወቅት እየሰሙ የዝሆን ጆሮ ይስጠን ፤ እያዩ አይኔን ግንባር ያድርገው እያሉ የሰነበቱት የወያኔ ባለስልጣናት የእንግሊዙ ባለስልጣን የሰጠነው ገንዘብ በአግባቡ ለተረጅው መድረሱን እናረጋግጣለን በማለት ከረርና ጠበቅ ያለ አቋዋም ይዘው መምጣታቸውን ሲረዱ በተራብ አንጀታቸው ከሆስፒታል አንስተው ምንም መጠለያ በሌለበት በረሀ ውስጥ የጣሉዋቸው ሲሆን ፤በዚህም የተነሳ ቀድሞም ደክመው የነበሩት ረሀብተኞች መሀከል ጥቂት የማይባሉት በአውላላ ሜዳ ላይ ህይወታቸው እንዳለፈ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች ያጋለጡ ሲሆን አሁንም ካፈርኩ አይመለሰኝ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት በወሰዱት አሳፋሪና አሳዛኝ እርምጃ ከመፀፀት ይልቅ እንዳላወቀና ምንም እንዳልፈፀመ መስለው ማውራታቸው እጅግ እንዳበሳጫቸው የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች ገልፀዋል።

ለርሀብተኛ ወገን የተላከውን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዩሮ እና ፓውንድ እነመለስ በሚስቶቻቸው ስም ግዙፍ ኩባንያ እየከፈቱበት ሲጠቀሙ ረሀብተኛውን ዘንግተው መልሰው «ማን ፈፀመው?» እያሉ በህዝብ እና በወገን ላይ እያላገጡ ከመሆኑም በተጨማሪ አይን ያወጣ እጅግ ድፍረት የተቀላቀለበት ወንጀል መፈፀማቸው እንዳሳዘናቸውም እነዚሁ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች ሲገልፁ ተደምጠዋል።

የእንግሊዙ ሚኒስትር ለተፈጠረው ረሀብ የወያኔን ቡድን ታጠያቂ ከማድረጋቸውም በላይ በቀብሪ ደሀር ሆስፒታል ውስጥ በርሀብ ተጎድተው በሞትና በመኖር መሀል ሲሰቃዩ የነበሩት ዜጎችን መደበቃቸው አሳፋሪው ወያኔ ያስፋፋው ርሀብ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን እንዳይተላለፍና እንዳይጋለጥ እንዲሁም ሚኒስትሩ እውነታውን እንዳያዩ ሆን ተብሎ በመለስ ትዕዛዝ የተወሰደ እርምጃ መሆኑን የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች ይገልፃሉ::

የእንግሊዙ ዓለማ አቀፍ ልማት ሚኒስትር ዳግላስ አሌክሳንደር በነመለስ ድርጊት በመናደዳቸው ወትሮም የነጣ ፊታቸውን ሚጥሚጣ አስመስለው የተፈጠረው ወንጀል በአለም አቀፍ ህግ ሊያስጠይቅ የሚችል ነው በማለት በመግለፃቸው የወያኔን መሪ መለስ ዜናዊን በማስደንገጡ ሆኖ ከሆነ አጣዳፊ እርምጃ እንወስዳለን በማለት እንዳላየና እንዳልሰማ ሆኖ ከመቅረቡም በላይ አዲስ ድራማ ለመስራት መጀመሩን የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች ገልፀዋል::

ለብዙ ቀናት ተዘዋውረው ይመለከታሉ ተብሎ ፕሮግራም የተያዘላቸው የእንግሊዙ ባለስልጣን በተፈፀመው ኢ- ሰብአዊ ድርጊት ከማዘናቸውም በተጨማሪ በመናደዳቸው የተነሳ ጉዞዋቸውን አጥፈው በመጡበት አኩዋሀን ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውንም የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ሰራተኞቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓት በኦጋዴን ፤በቀብሪደሀር፤ በደገሀቡር ፤በፌርፌር፤ በቀላፎና በሌሎችም የሱማሌ ክልል አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመዝነቡ የተነሳ ለህዝቡ ትንፋሽ ይሰጣል ተብሎ የነበረ ቢሆንም በተፈጠረው በሽታ ቀድሞ ከነበረው ረሀብ በላይ ህዝቡን እየፈጀ መሆኑን እነዚሁ የለጋሽ ድርጅት ሰራተኞች ገልፀው መድሀኒት አቅርቦት እንኩዋን እንዳይደርስ ታጣቂ ኃይል በአካባቢው ስላለ ሊገድሉዋችሁ ይችላል እያሉ የወያኔ ወታደሮች እየከለከሉ ህዝቡ በአጣዳፊ በሽታ እንዲያልቅ ሆን ብለው እየሰሩ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

በእንግሊዙ ባለስልጣን ቁጣ የተደናገጠው መለስ ዜናዊ ድርጊቱን የፈፀሙት የክልሉ ባለስልጣን ናቸው ለማሰኘት ከአንድ ወር በፊት ከስልጣን በተባረሩት የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንትና ካቢኔው ላይ ለማላከክ አዲስ ድራማ እየሰራ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች በቅርቡ እርምጃ ወስጃለሁ በማለት ለእንግሊዝ ጌቶቹ ለማሳመንና የተከለከለውን የእርዳታ ፓውንድ ለመውሰድ የታቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል ሲሉ እነኚሁ የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች ገልፀዋል::

በዚህም መሰረት በቅርቡ የሱማሌ ክልል ፕሬዝደንት ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር መሪዎች ጋር ግንኙነት አለህ በሚል ከስልጣኑ አንስተው ከጅጅጋ አዲስ አበባ አምጥተው የቁም እስረኛ እንዲሆን ያደረጉት ከመሆኑም ባሻገር የእሱን ካቢኔዎች በሙሉ ከስልጣናቸው አንስተው እስከአሁን ማንም ያልተሾመበት ቢሆንም ከአዲስ አበባ ከደህንነት ቢሮና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የተውጣጣ አንድ ቡድን ወደ ጅጅጋ ተጉዞ እያስተዳደረ እንደሚገኝ የገለፀው የደረሰን ዘገባ በቀብሪ ደሀር ሆስፒታል ድርጊቱ የተፈጸመው መለስ በሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት መሆኑን እና ለዚህም ጥፋት ተጠያቂዎቹ የተባረሩት የሱማሌ ክልል ርዝራዦች ነው በሚል እቅድ መንደፉንና እንቅስቃሴ መጀመሩን አጋልጠዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሱማሌ ክልል ውስጥ የክልሉ መንግስት ያልተቋቋቋመ ቢሆንም ከአዲስ አበባ በተላኩ የህወሀት ሰዎች እየተመራ ሲሆን የፖሊስ ኃይሉንም ለማጠናከር በሚልም የወያኔው ተላላኪ ወርቅነህ ገበየሁ በጅጅጋ ከተማ ከርሞ እንደተመለሰ ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኦጋዴን ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ጥቃት እየደረሰበት ያለው የወያኔ ጦር ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመምጣቱ የተነሳ የክልሉ ባለስልጣናት ተመሳጥራችሁ ነው ጥቃቱን የምትፈፅሙት በሚል ከስልጣናቸው ቢባረሩም ጥቃቱ እንዳላቆመና ይልቁንም በብዙ ቦታዎች እየተስፋፋ በመሄዱ ወያኔ ባደረበት ፍርሀት የተነሳ ግዙፍ ጦር በአካባቢው ማስፈሩን ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

እንደ ውስጥ እግር ቁስል አላላውስ ያለው የኦጋዴን አካባቢ ጥቃት አንዴ በአየር ሌላ ጊዜ በእግረኛ እና በሜካናይዝድ የተደገፈ አሰሳና ውጊያ ቢያደርግም ያሰበው ያልተሳካለት ወያኔ የክልሉን ህዝብ በመጥላቱና በመጠራጠሩ የተነሳ በርሀብ እና በእንግልት እንዲያልቁ እያደረገ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ አሁንም ድረስ እርዳታ ወደ አካባቢው እንዳይንቀሳቀስ የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን እየፈጠረ ያለው እርዳታው ለታጣቂ ይደርሰዋል የሚል ግምት ስላለው መሆኑንም ዘገባው አስረድቶዋል::

የእናቲ መቀነት አደናቀፈኝ የሚለው ወያኔ ህዝቡ ተርቦ የእለት ጉርስ ሲጠይቅ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ነው እያለ ለማታለል ደፋ ቀና የሚል ቢሆንም ያሰበው ሳይሆን ፤የጀመረው ውጥን ሳይሳካለት በእንጥልጥል ብቻ እየተወ ሲሆን፤ በተለይም በሱማሌ ክልል ውስጥ ባሳለፍነው ዓመታቶች 10 ፕሬዝዳንቶችን እንደ ውሀ ቀጂ ያፈራረቀ መሆኑንና ለዚህ ዋነኛው ምክንያቱ ደግሞ እራሱን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ብሎ ከሚጠራው ታጣቂ ኃይል ጋር ንክኪ አላቸው ከሚል ጥርጣሬ የመነጨ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

የሰሞኑ የወያኔው የፌዴራል ፖሊስ አዘዥ ወርቅነህ ገበየሁም የጅጅጋ መሰንበት ዋነኛው ምክንያት የአካባቢው ተወላጅ ፖሊሶች ላይ እምነት በማጣቱ ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ የሱማሊኛ ቁዋንቁዋ የሚናገሩትን ሰብስቦ ወስዶ ከተወላጅ ፖሊሶች ጋር ለማገናኘትና የስራ መመሪያ ለመስጠት መሆኑን ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::